የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

**OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ሃያ አራተኛ ዓመት ቁጥር ፵፭
አዲስ አበባ ሰኔ ፲፭ ቀን ፪ሺ፲ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

24th Year No. 45
ADDIS ABABA 22nd June , 2018

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፹፮/፪ሺ፲ ዓ.ም

ለኢትዮጵያ ኤሌክትሪፊኬሽን ፕሮግራም ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከዓለም አቀፍ የልማት ማህበር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ......................................................ገጽ ፲ሺ፫፻፹፰

## Content

Proclamation No. 1086/2018

**International Development Association Financing Agreement for financing the Ethiopia Electrification Program Ratification Proclamation** ……………………….Page 10388

### አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፹፮/፪ሺ፲

### በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በዓለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

ለኢትዮጵያ ኤሌክትሪፊኬሽን ፕሮግራም ማስፈጸሚያ የሚውል ፩፻፸፮ ሚሊዮን ፱፻ ሺ ኤስ.ዲ.አር (አንድ መቶ ሰባ ስድስት ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ሺ ኤስ.ዲ.አር) መደበኛ ብድር እና ከስኬል-አፕ ፋሲሊቲ ክሬዲት ፩፻፳፭ ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር (አንድ መቶ ሃያ አምስት ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር) የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በዓለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል የካቲት ፴ ቀን ፪ሺ፲ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ግንቦት ፳፫ ቀን ፪ሺ፲ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭(፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፦

### PROCLAMATION No. 1086/2018

### A PROCLAMATION TO RATIFY THE FINANCING AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE INTERNATIONAL DEVELOPMENT ASSOCIATION

**WHEREAS**, a Financing Agreement, between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association stipulating that the International Development Association shall provide to the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia a Loan amount of 176,900,000 Special Drawing Rights (One hundred seventy six million Nine hundred thousand SDR) Regular Credit; and $125,000,000 (one hundred twenty five million United States Dollar) from Scale- Up Facility Credit for financing the Ethiopia Electrification Program was signed in Addis Ababa on the 9th day of March 2018;

**WHEREAS**, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Financing Agreement at its session held on the 31st day of May 2018;

**NOW, THERFORE,** in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

**፩. <u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ አዋጅ "ለኢትዮጵያ ኤሌክትሪፊኬሽን ፕሮግራም ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከዓለም አቀፍ የልማት ማህበር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፹፮/፪ሺ፲" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**፪. <u>የስምምነቱ መፅደቅ</u>**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በዓለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል የካቲት ፴ ቀን ፪ሺ፲ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረሙት የብድር ስምምነቶች ቁጥር 6158-ET (Regular Credit) እና 6157- ET (Scale Up Facility Credit) የብድር ስምምነቶች ፀድቀዋል።

**፫. <u>የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ሥልጣን</u>**

የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፩፻፸፮ ሚሊዮን ፱፻ ሺ (አንድ መቶ ሰባ ስድስት ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ሺ ኤስ.ዲ..አር) መደበኛ ብድር እና ከስኬል-አፕ ፋሲሊቲ ክሬዲት ፩፻፳፭ ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር (አንድ መቶ ሃያ አምስት ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል።

**፬. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

**ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።**

**አዲስ አበባ ሰኔ ፲፭ ቀን ፪ሺ፲ ዓ.ም**

**ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ**

**የኢትዮጵ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**1. <u>Short Title</u>**

This Proclamation may be cited as the "International Development Association Financing Agreement for financing the Ethiopia Electrification Program Ratification Proclamation No.1086/2018".

**2. <u>Ratification of the Agreement</u>**

The Financing Agreement Number 6158-ET (Regular credit ) and 6157-ET (Scale Up Facility Credit) signed in Addis Ababa on the 9th day of March 2018 between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association is hereby ratified.

**3. <u>Power of the Ministry of Finance and Economic Cooperation</u>**

The Ministry of Finance and Economic Cooperation is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Loan amount of 176, 900,000 Special Drawing Rights (One hundred seventy six million Nine hundred thousand SDR) Regular Credit; and $125,000,000 (one hundred twenty five million United States Dollar) Scale- Up Facility Credit in accordance with the terms and conditions set forth in the Financing Agreement.

**4. <u>Effective Date</u>**

**This Proclamation shall enter into force on the date of its publication in the Federal Negarit Gazette.**

**Done at Addis Ababa, this 22nd day of June 2018.**

**MULATU TESHOME (DR.)**

**PRESIDENT OF THE FEDRAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**